## ሲሆን መርዳት ካለዚያ ማፈርን ምን አመጣው?

በድምጽ ማሰራጫ ጣቢያዎች በሚቀርቡ ዜናዎች ላይ የቀረቡ ተቃውሞዎች፣ በሚል ርዕስ የቀረበውን በእንግሊዘኛ የተጻፈውን ጽሑፍ በታላቅ ተመስጦ አነበብኩት። የጽሁፉ ዓላማ በሃገራችን በኢትዮጵያ በብዛት ተስፋፍቶ የሚገኘውን የፊስቱላ (የማህጸን መደባለቅ) በወጣት ሴቶች ላይ የሚያመጣውን እጅግ አሳዛኝ ጉዳትን ለመከላከል፤ የሚደረገውን ጥረት በብዛት ለ ማሳወቅና የገንዘብ እርዳታ ለማሰባሰብ በኦፕራ ዊንፍሪ የቴሌቭዥን መርሃግብር ላይ መቅረቡን ኢትዮጵያውያን መቃወማቸውን የሚያሳውቅ ነው። ለዚህ መጣጥፍ መነሻ የሆነኝን መልእክት ያገኘሁት http://www.aesed.org/ Controversies Over Ethiopian women in the media ለሁላችንም ለውይይት እንዲመቸን ስለፈለግሁኝ በራሳችን ቋንቋ ብመልስ ቅር እንደማትሰኙ ተሰፋ አለኝ።

እንግዲህ ውስጥ ውስጣችን ወይም በምንኖርበት አካባቢ የሚያጋጥመንን የግል ገጠመኝ እንዲህ አደባባይ ወጥቶ እንድንወያይበት አጋጣሚው ሲገኝ እሰየው ነውና በዚህ አጋጣሚ የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅትን(ዓኢሴድ)ይህንን ወቅታዊ፤ አስተማሪ የሆነ ጽሑፍ እንድናነብ ስለጋበዘን በቅድሚያ አመሰግናለሁ። ነገር ግን አንብበን ዝም የምንለው ነገር ወይም አንብበን በመረጃነት ብቻ ልንቀበለው የማንችለው ነገር በመሆኑ ይህንን መጣጥፍ የምናነብ ሁላችን ወደ ውይይት በመቀየር ነገሩን ትኩረት ሰጥተን እንድንወያይበት አጥብቄ አሳስባለሁ።

እንደሚታወቀው ሁኔታዎች በትክክል መካሄድ ባለበት የኅብረተሰብ መዋቅር አንድን ችግር ችግርነቱን መጀመሪያ መረዳት፤ ከዚያም ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሄ እና ቋሚ መፍትሄ ብሎ በመከፈል ችግሩ ጨርሶ የሚወገድበትን መንደፍ ከዚያም በተግባር ማዋል የተለመደ አሠራር ነው። ፊስቱላ በሃገራችን ሴቶች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ትኩረት ተሰጥቶት የመጀመሪያው ህክምና መሰጠት የተጀመረው ከሰላሣ አምስት ዓመታት (ግምት ነው) ያህል ሲሆነው ዓላማው ለጊዜው በህመሙ የሚሰቃዩትን ሴቶች ለማዳን ነበር።የጉዳቱ ተጠቂ የሆኑትን ሁሉ ማከም ስለማይቻል በ100,000 የሚቆጠሩ ሴቶች እየተሰቃዩ ይገኛሉ በየዓመቱ ቢያንስ 9,000 ያህል ወጣት ሴቶች የፊስቱላ ጉዳት ተጠቂዎች ናቸው። እንግዲህ እንደማገኘውም የሦስተኛ ዓለም ሃገር ሃገራችን እንኳን የዚህን ችግር ዘላቂ መፍትሄ መስጠት ይቅርና በየጊዜው የችግር መፈልፈያና የሰው ልጅ በሰውነቱ ከባድ ፈተናዎችን የሚፈተንባት ሃገር እንደሆነች ሁላችንም ምስክር ነን። ባይሆን ኖሮ አሁን ባለው የዘመናዊ ህክምና ድጋፍ፤ የበሽታው አመጣጥና መከላከያ ዘዴው በቂ መረጃ በሞላበት ወቅት በዚህ ተጠቂ የሚሆኑ እህቶች ባልኖሩን ነበር።

ፊስቱላ የሚባለው አካላዊ ጉዳት የሚደርሰው አንዲት ሴት ልጅን ለመውለድ ምጥ ላይ በተያዘች ግዜ የህክምና እርዳታ በሌለበት ቦታ የምጡ መቆየት ወይም የጽንሱ ከተፈጥሮ የአወላለድ ውጭ (የተለያዩ የህክምና መግለጫዎች ሊኖሩት ይችላል) ሲሆን በማህጸንዋና በውስጣዊ ብልቶች መካከል የሚፈጠር ቀዳዳ ነው። ይህ ቀዳዳ ወዲያውኑ ህክምና ካልተደረገለት ወደ ቁስልነት (ኢንፌክሽን) በመቀየር የተለያዩ ፈሳሾችን በማመንጨት ሴቲቱ በኅብረተሰቡ ውስጥ በነጻነት መመላለሷን እስከ መንፈግ የሚያደርስ እጅግ አሰቃቂ የአካል ብቻ ሳይሆን የሥነ-ልቡና ቀውስ የሚያስከትል አደጋ ነው።

በነገራችን ላይ የፊስቱላ በሽታ የኢትዮጵያ እናቶች ብቻ ችግር ሆኖ መታየት የለበትም። በአውሮፓና በአሜሪካ እስከ 20ኛው ምእት አጋማሽ ድረስ ሴቶችን ሲያጠቃ የነበረ በህክምና

ሊከላከሉት የሚቻል ተከላክለውም ሙሉ በሙሉ ያስቀሩት አደጋ ነው። በታዳጊ ሃገሮች ግን አሁንም ችግሩ እጅግ የጎላ ነው።

ለምን በኢትዮጵያና በሌሎች ታዳጊ ሃገሮች ጎልቶ ይታያል የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት፤

- ሴት ልጅ ከሕጻንነት ጀምራ በምታድግበት ወቅት በቂና የተመጣጠነ ምግብ ባለማግኘት ምክንያት የተፈጥሮ አካሏ (ማህጸንና የፔልቪስ አጥንት) የሚባለው ጭምር ሕጻንን ለመሸከም እንደሚያስችል ሆኖ አለማደግ ( Stunt growth)፤
- ይህ በተገቢ ሁኔታ ያላደገው የማህጸን አጥንት በምጥ ሰዓት ችግር ስለሚፈጥር
- ሴቶች ልጆች በለጋነት እድሜ ልጅ እንዲወልዱ መደረግ፤
- እንዲሁም ወላዶች በእርግዝና ወራትና በወሊድ ጊዜ ህክምና አለማግኘታቸው ለአደጋው መስፋፋት አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ጥቂቶቹ ምክንያቶች ናቸው።

እንግዲህ መነጋገሪያ የሆነን ይህ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከል ከደረሰም በኋላ ማዳን የሚቻል ግን እጅግ ዘግናኝ የሆነ ጉዳት በእህቶቻችን ላይ ሲደርስ ዝም ብሎ ማየት ያልተቻላቸው ወገኖችም ሆኑ የውጭ ሃገር የእርዳታ ሰዎች/የህክምና ባለሙያዎች ጭምር ሲከላከሉ እስከ አሁን ቆይተዋል። ላለፉት ሰላሣ አምስት ዓመት ማለት ነው። ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ችግሩ በሁለት ይከፈላል፤ ጊዚያዊ (ጉዳቱ የደረሰባቸውን ሴቶች በህክምና ማዳን) ከችግሩ ሙሉ በሙሉ የመዳን እድሉ 90% ያህል ነው። የዘለቄታው መፍትሄ ግን ሃገራችንን ካለችበት የችግር መቀመቅ በማላቀቅ የወደፊት ሃገር ተረካቢ የሆኑ ሕጻናት በተመጣጠነ ምግብ እንዲያድጉና ኅብረተሰቡ በልጅነት እድሜ ወደጋብቻ መሄድ የሚያመጣውን ጉዳት ተገንዝቦ ሴቶች ልጆቹን እንዳይድር ማድረግ ናቸው።

አውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደምንሰማውና እንደምናየው አፍጥጦ የሚታየውን ችግር እንደሌለ አድርጎ ለመሸፋፈን መሞከር በየዋህነትም ይደረግ በሌላ ተልእኮ ተቀባይነት የለውም። ለምሳሌ ከምእራባውያን ሃገሮች ኢትዮጵያ ደርሰው መጥተው የሸራተንን ሆቴል የተመለከቱ የዋሃን በሙሉ ልብነት«ኢትዮጵያ ተለውጣለች፤ ችግር የለም፤ የተጋነነ ወሬ ነው» እንደሚሉት ነው ማለት ነው። በእንደዚህ ያለ መሰረትንት በሌለው ስሜታዊ ግንዛቤ ምክንያት የድሆችና የድምጽ አልባ ሰዎች (ሴቶች) ሰብአዊ መብት የመኖር መብት መነፈግ የለበትም።

በአንድ ወቅት በሥራ ቦታዬ ላይ ያጋጠመኝን ላካፍላችሁ።
አንድ ቀን የሥራ ባልደረቦቼ ከሁለት አሜሪካውያን ጋር ቆመው ያወራሉ። ምን እንደሚያወሩ ለመረዳት ብዙ ከመድከሜ በፊት የሥራ ባልደረባዬ የሆነችው የሀገሬ ልጅ ጠራችኝና እኔም ወደ ውይይቱ ተቀየጥኩኝ። አሜሪካዊው ወጣት እድሜው ከ25 አያልፍም። የጎት ተከታይ ስለ ሆነ አንዳንድ የሚያደርጋቸው ልብሶችና በሰውነቱ ላይ ያለው የጌጣጌጥ ብዛት ከሌለው ሰው ለየት ብሎ እንዲታይ የግድ ይላሉ። ይህንን ልማዱንም ለማስፋፋት በተለይ የአፍሪካ ጎሳዎችን ማጥናት በጣም ይወዳል። ከነዚህም የማሳይ፤(ኬንያ) የጆሮ አበሳሳቸው በጣም ስለሚማርከው ስለነሱ በጣም ብዙ ያነባል፤ እንግዲህ ይኸ ፍላጎቱ ነው መሰል ወደ ኢትዮጵያውያን

የኮንሶ ብሄረሰቦች የመራው በዚያን ዕለት ፎቶግራፍ ይዞ በመምጣት የምናውቀውን እንድንነግረው ሲጠይቅ ነበር እኔ የደረስኩት፣http://www.jahodapetr.com/gallery_1.phpለካስ የሥራ ባልደረባዬ ከንፈሩ በሸክላ የተለጠጠውን የኮንሶ ጉብል ስታይ ይሄ ኢትዮጵያዊ አይደለም በማለት ላቧ ጠብ እስኪል ለማስረዳት ትሞክራለች። እየደጋገመች የምትለው ነገር ቢኖር ግን ያው ነው። “No Ethiopian” ከእኔ ጋር ብዙ ግዜ በአፍሪካ ስለሚገኙ ጎሳዎች ባህል ውይይት ስለምናደርግ ጠርቶ ሲጠይቀኝ በአይኗም በአፏም በእጇም እየተናገረች «ሀበሻ አይደሉም በይ» ትላለች። ይህ ከንቱ ጥረቷ

እጅግ አስገርሞኝ ለአፍታ ሳያት ቆየሁና ወደ ፎቶግራፉ በመመልከት ኢትዮጵያዊ መሆናቸው
ንና የማውቀውን ያህል ስለባህላቸው ለማስረዳት ሙከራ አደረኩ። እውነቱን ለመናገር እኔም
በዜና ማሰራጫ ከመስማት የበለጠ ስለነዚህ ጎሳዎች የማውቀው ብዙም የለም። በእርግጠኝነት
የማውቀው ነገር ቢኖር አንድ ነው። በእኔ ውስጥ የሚፈሰው ኢትዮጵያዊ ደም በእነሱም
ውስጥ እንደሚፈስ ነው ይህ ለኔ ከምንም የበለጠ አጥጋቢ ነገር ነው። የሥራ ባልደረባዬ ለመ
ጨረሻ ጊዜ ያነጋገረችኝ ቀን ሆነ። የምትለው ነገር ተገቢ እንዳልሆነና እርማት እንድታደርግ
በተደጋጋሚ ለማስረዳት ብሞክር «አዋረድሽን» ከማለት ሌላ ሌላ አርኪ መልስ ልትሰጠኝ
አልቻለችም። ይህ ዓይነቱ አመለካከት እጅግ የተሳሳተና መከፋፈልን ዘረኝነትን የሚያስፋፋ
በመሆኑ እርምት ያስፈልገዋል። አንድ በሉልኝ። በራስ ሰንካላ ሚዛን እየመዘኑ ኢትዮጵያን
የምታክል ታላቅና በልጆቿ ባህል ያሸበረቀች ሃገር ግለሰቦች ዜግነቱን እንደራሳቸው ሃብት
በመቁጠር ለወደዱት ሊሰጡ ለጠሉት ሊነፍጉ? ይሄ ታዲያ የሕዝብን ክብር መግሰስ አይደለም?

ለመሆኑ አኩሪ የዜግነት መለያ ምንድነው?
አንድ ሕዝብ የዜግነት መለያ ብሎ ለራሱ መርጦ የሚያከማቻቸውና ባስፈለገ ግዜ ለመውረግረ
ጊያ፤ ለመመኪያነት፤ ለመለያነት የሚጠቀምባቸው ልዩ የሚያደርጉ ምልክቶች ከዘመን ብዛት
ያበጃል፤ ይህ ሰንደቅ ዓላማውን ይጨምራል ማለት ነው። የብሄራዊ ምልክቱ ነውና። ነገር
ግን ኅብረተሰብ እየደረጀ አንዲት ሃገር ለዘመናት የሰዎች መኖሪያ የትውልድ መተላለፊያ ሆና
ስትኖር ደግሞ ተፈጥሮ ከሰጣትም ሆነ ልጆቿ በጥረት ካፈሩት አኩሪ ታሪክ ጎን ለጎን ባህል
የሚያመጣቸው፤ በኑሮ ጫና ምክንያት፤ ወይም ደግሞ በወቅቱ የዘመናዊነት መስፈርት ሲለኩ
የተለመዱ ግን አሳፋሪ ባህሎች፤ ጎጂ ባህሎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ይዳብሩና ሲቻል እየተሸ
ፈኑ ሳይቻል ደግሞ ብቅ እያሉ ይኖራሉ። ለምሳሌ ኢትዮጵያ የሰሜን ቀበሮ፤ ዋልያ፤የመሳሰሉ
የዱር አራዊት በኢትዮጵያ ብቻ ስለሚገኙ የብሄራዊነት መኩሪያ ናቸው። ቡና ለመጀመሪያ
የተገኘባት ሃገር በመሆንዋ «የኢትዮጵያ ቡና» ሲባል ኩራት ይሰማናል። ኢትዮጵያ የጀግኖች
ሃገር ሆና ኖራለችና የአድዋ፤ የማይጨው ድል ሲነሳ ከተቀመጥንበት ያቁነጠንጠናል፤ ድምጻ
ችንን ከፍ አድርገን «እኔ እኮ ኢትዮጵያዊ ነኝ» ልንል ይቃጣናል። እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ
ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

ታዲያ ከዚሁም አንጻር ጎጂ ባህላችን ወይም በኋላ ቀርነት ምክንያት፤ በድህነታችን ምክንያት
ያለብንን የወገን ጉስቁልና ስለምን እናፍርበታለን? ለመሆኑ ከጣቶቻችን አንዱ ቁስል ቢኖርበት
ይህ የኔ አካል አይደለም ልንለው እንችላለን? በሃገራችን በኢትዮጵያ በተለይ ባለባቸው የመደ
ብና የጾታ ጭቆና ምክንያት የራሳቸው የሆነ ተሰሚ ድምጽ የሌላቸውን እህቶቻችንን የሚደር
ስባቸው አሰቃቂ በደል ወደአደባባይ ወጥቶ ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ጩኸታቸውን ጮኸን
መፍትሄ እንደመፈለግ እንዴት እናፍርባቸዋለን? እንዴትስ ለሚደርስባቸው ልክ የሌለው በደልና
ግፍ ከፊት ቀድመን ልንጮህላቸው ስንችል ተመችቶን በየምእራቡ አለም የምንኖረውን የስም
ብቻ ኢትዮጵያውያን ክብር ያጎድፋሉና ችግራቸው ለዓለም መሰማት የለበትም እንላለን?
በእውነት እጅግ የሚገርም ነገር ነው። አለባብሰው ቢያርሱ፤ በአረም ይመለሱ ነው።

ምንጩ የኛ የሆነውን ተረት በገላጭነቱ ለመጠቀም እንደሞከርኩት አንድ ሕዝብ በውስጡ
ያለውን ችግር አውጥቶ ካልተወያየበትና መፍትሄ ሊሰጥበት ካልተዘጋጀ ዋለም አደረም ችግሩ
ፈጦ ከአደባባይ የወጣ ዕለት የዜግነት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በሃላፊነት የተቀመጡትም
ሆነ ማንኛውም ዜጋ ከታሪክ ተወቃሽነት ሊድን አይችልም። በብሄራዊ ምልክቶቻችን እንደተ
መካን ሁሉ እነኚህን የብሄራዊ ምልክት ነጸብራቅ የሆኑ ወገኖቻችንን እንዴት ከችግር አድነን
የኩራቱ ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ ሳንተልም መቀመጥ እንመኛለን?

ሃገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት፤ በተለይ በሴቶች ላይ በሚደርሰው በደልና ግፍ እስከወዲያኛው ትውልድ እንደ ቅርስ የሚተላለፍ ቁስልና አሻራ እያከማቸች ትገኛለች። ጥቂቶቹን አሳሳቢ ችግሮች እስቲ እንመልከት፤

- በሴተኛ አዳሪነት ራሳቸውን ለዕለት እንጀራ ሲሉ አዋርደው የሚኖሩ እህቶቻችን ቁጥር ጉቦ፤ ቅሚያና የሥልጣን ዋልጌነት በበዛበት የአስተዳደር መንግስት ቁጥሩ በሚያስጋ ሁኔታ እየጨመረ ነው፤ ይህንንም ለማስቀረትም ሆነ መፍትሄ ለመፈለግ የምናደርገው ጥረት ከቁጥር የሚገባ አይደለም።

- በቀሳፊው ኤይድስ ምክንያት የሚቀሰፉት ወገኖቻችን ቁጥር እጅግ በርካታ ነው። የሴቶችና የሕጻናት ቁጥር ላቅ ያለውን ቦታ ይይዛል። ሌሎች ተመሳሳይ ችግር ያላቸው የአፍሪካ ሃገሮች በበቂ በመደራጀታቸውና የበሽታውን አደገኛነት ሕዝባቸውን ሳያሰልሱ በማስተማራቸው የቀሳፊነቱን ቁጥር ለመቀነስ ችለዋል። እኛ ምን እያደረግን ነው? የትኛውንስ ደብዳቤ ለኮንግረስ አባሎቻችን ለፓርላመንት ተወካዮቻችን ጽፈን ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተን ተገቢው የሆነ ትኩረት እንዲሰጠው ቅስቀሳ በማድረግ የበኩላችንን ድርሻ የተወጣነው?

- በጽሁፉ ላይ እንደተጠቀሰው በየአረብ ሃገሩ ከባርነት ላልተናነሰ የጉልበት ብዝበዛ አልፈው እየተሰጡ አካላቸው እስከ መጉደል፤ የሥነ ልቦና ቀውስ እየደረሰባቸው፤ በተስፋ መቁረጥ ህይወት እስከማጣት እንዲሁም በቀጣሪና በአስቀጣሪዎቻቸው እየተደፈሩ ልጅ ያለ አባት የሚያሳድጉ እህቶች ቁጥር ከመቼውም በበለጠ እየጨመረ ነው። በሌሎችም የስደት ቦታዎች ሁሉ የሚንገላቱ ወገኖቻችን የኛን ለፍትህ መጮህ የሚጠባበቁ ሆነው ይገኛሉ። እኛ ግን እጃችንን አጣምረን ስንችል ከንፈር እየመጠጥን ሳንችል ደግሞ እንዳላየ በመሆን ብቻ ነው የምናልፈው።

- በልጅነት እድሜያቸው በሚደርስባቸው ግርዛት በበሽታ የሚለከፉ ሴቶች ሕጻናት አሁን ባለንበት ዘመን እንኳን አለመቀነሱ ለሁላችንም አሳፋሪ ነው፤

- ገና በለጋነት እድሜያቸው በቤተሰብ ስምምነት በሚደረግ ትዳር በመጠመድ ልጅ የመውለድ አቅም በማጣር የሚደርስባቸው የማህጸን መደባለቅ (ፌስቱላ)Fistula
የሚሰቃዩ ለሁለተኛም ጤናማ ህይወት ለመምራት የሚቸግራቸው በሺህ የሚቆጠሩ እህቶቻችን ናቸው።

- በልጅነት እድሜያቸው የትምህርት እድል በማጣት የመሀይምነት ጨለማ ውስጥ ተዘፍቀው የኑሮን ሸክም ከእለት እለት ብቻ ለመግፋት ህይወታቸው የተወሰነ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ናቸው።

- በባሎቻቸው ወይም በማንኛውም ወንድ የጾታ ጥቃት የሚደርስባቸው ይኸም በኅብረተሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ የሚያሰጣቸውና በተስፋ መቁረጥ የተከበበ የጨለማ ህየወት የሚገፉ እጅግ ብዙ እናቶች/እህቶች ናቸው። ለነዚህ የህግ ጥላነት እንዲደርሳቸው የሚደርገው ጥረት አናሳ ነው።
- አለአስፈላጊ ጽንስን ለማሰወገድ በባህላዊ መንገድ በመጠቀም ህይወታቸውን የሚያጡና በሽተኛም ሆነው የሚቀሩ በጣም ብዙ ናቸው። ወዘተ.......

ሌላም ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። ሃገራችን ኢትዮጵያ በነዚህ ከላይ በተጠቀሱ ችግሮች ዘርፍ ሁሉ የቀዳሚነትን ደረጃ ይዛ ትገኛለች ብል የግል አመለካከቴ አይሆንም። ካስፈለገ በመረጃ የተደገፈ ጽሁፍም ማቅረብ ይቻላል። ታዲያ እነኚህ ችግሮች ችግሮች መሆናቸው የገባን ሁሉ እንዴት ዝም ብለን መቀመጥ እንችላለን? እኛስ ምንም ለማድረግ

አቅም የለንም በማለት የተለያዩ ምክንያቶች ልንደረድር እንችላለን ነገር ግን ኅብረተሰብ ያስከተለው ችግር ሰለባ የሆኖ ዜጎቻችንን ሊረዱ የሚመጡ ሰዎች ፊት እንዴት በእንቅፋትነት እንቆማለን? ይህንን ስል በምእራቡ ዓለም የዜና ማሰራጫዎች ሁሉ የሚቀርቡ የኢትዮጵያ ወይም በአጠቃላይ የሦስተኛ ዓለም ሃገሮች ችግር እንደ መለመኛ ምክንያት አይወሰዱም ማለቴ አይደለም። ግን ወገኔን መለመኛ አታደርጉም ብሎ የቀረቀረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ግን ዛሬ ነገ ሳይል በሚችለው አቅሙ፤ ሙያው በሚፈቅድለት መስክ እየተሰማራ ያለውን ችግር ለመግፈፍ በየአቅጣጫው ሊሰለፍ ያስፈልጋል። ወይ አይገቡ ወይ አያስገቡ እንደተባለው በር ላይ መቆም ተገቢ አይደለም። ከውስጥ ሆነው በአፈና የተቀመጡትንም ድምጽ እንዳይሰማ መከልከል ሰብአዊ መብትን የሚጋፋ ወንጀል ነው እላለሁ።

ለተገፉ/ድምጽ ለሌላቸው እህቶቻችን መብት መቆምን ባህል አድርገን እንያዝ ትክክለኛ ነገር ነውና።

ሐረገወይን ስለሺ።
ጥር ፲፬-፳፻፩ ዓ.ም